# የሚያድግ ኢኮኖሚ ነገር ግን የማይታይ የማይዳሰስ !

## መግቢያ

ሰሞኑን በአዲሱ ዐመት የፓርሊያሜንት መክፈቻ ንግግራቸው ላይ የኢህአዴግ ፕሬዚደንት አቶ ግርማ ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት ስድስት ዐመታት ከአስር በመቶ(10%) በላይ እንዳደገ ሲያበስሩ ፣ እንደዚህ ዐይነቱ ዕድገት በምዕራቡ ኢኮኖሚ ውስጥ እንኳ ሊደረስበት ያልተቻለ እንደሆነ በደስታ ገልጸዋል። ይህ ዐይነቱ ዕድገት ሊታይ የቻለው የዓለም ኢኮኖሚ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚገኝበት ወቅትና ፣ እንዲሁም ደግሞ የውስጥ ችግር ከፊታችን ላይ ተደቅኖ በምንገኝበት ወቅት ሲሆን ፣ አዎንታዊ ውጤቱ የያዝነውን የኢኮኖሚ ዕድገት ፈለግ የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል።  ይህ ዕድገት በአዲሱ ዐመት በዚህ መልክ እንደሚቀጥል ሲያስረዱ ፣ የዋጋ ግሽበትም ከአስር በመቶ በታች ዝቅ እንደሚል አብስረውልናል።

በአለፉት አስር ዐመታት በጠቅላይ ሚንስተሩና በፊናንስና በኢኮኖሚ ዕድገት ሚንስተራቸው በአቶ ሱፍያን አህመድ ፣ እንዲሁም ደግሞ አገዛዙን በሚደግፉትና በልዩ ዓለም ውስጥ የሚኖሩት ፣ በየፓል ቶክ ውስጥ የሚደነፉት ጀግኖች ፣ አገራችን ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ዕድገት የሚታይባት አገር እንደሆነችና ህዝቡም በኑሮው እንደተሻሻለ ሲምሉ ሲገዘቱ ይሰማል። በተለይም ደግሞ ፣ አዲስ አበባ እዚህና እዚያ የተተከለው ህንፃና የመጨፈሪያ ቤት የአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት ምልክት ሆኖ የሚታያቸውና ፣ ይህንን በቪዲዮ በመቅረጽ ሊያሳምኑን የሚሞክሩት ፣ እዚያው በዚያው ደግሞ ሺህ በሺህ የሚቆጠረው ህዝባችን በድህነት ዓለም ውስጥ ዘፍቆ በመኖር የዕለት ምግቡን ከቆሻሻ እየለቀመ እንደሚበላ በመካድ ነው። አገር ቤት በየዐመቱ እየተመላለሱ ከጉብኝት ሲመለሱ ስለአገራችን ሁኔታ ከሚነግሩን እህቶቻችንና ወንድሞቻችን የምንሰማው ግን በስታትስቲክስ ከተደገፈ ማስረጃ ሺህ ጊዜ እንደሚበልጥና ፣ ስለሁኔታውም አስከፊነት አንድ የኢኮኖሚ ምሁር ነኝ ባይ ከሚል የበለጠ እየዘረዘሩ የሚነግሩን እንደ ህያው ማስረጃ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል። የእነዚህ እህቶቻችን አገላለጽ አንድ ፈላስፋ እንዳለው ዐይነት ማስረጃ ነው። ይኸውም ስለአንድ የተመሰቃቀለና የተበላሸ ሁኔታ ብዙ በቲዎሪና በቁጥር በተደገፈ ማስረጃ መግለጽ አያስፈልግም ፤ ምክንያቱም እራሱ በሁለት ዐይንህ የምታየው ሁኔታ በቂ ማሰረጃ ስለሆነ ነው በማለት የገለጸው  ዐይነት ሁኔታ ነው። የሚደረገውም ትግል ይህንን የመሰለ የተጨማለቀ ሁኔታ ተቀብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ፣ ወይም ደግሞ የለም በዚህ አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ መኖር የለብኝም ብሎ ቆርቶ ተነስቶ ታሪክ በመስራትና ባለመስራት መሀከል የሚደረግ ትግል መሆን አለበት ወይም የለበትም ነው ጥያቄው። ስለዚህም ፣ የአገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት በዚህ ዐመት በዚህ መጠን ጨምሯል ፣ አልጨመረም እያሉ ሙግት ውስጥ እምብዛም መግባት የሚያስፈልግ አይደለም። ምክንያቱም ስለአንድ አገር ዕድገት በቁጥር ከተደገፈ ማሰረጃ ይልቅ ሁኔታው የበለጠ በቂ ማሰረጃ ስለሚሆን ነው። በሌላ ወገን ደግሞ በኢኮኖሚ ዓለም ውስጥ የሚያወናብዱ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የብዙ አፍሪቃ አገር ኢኮኖሚዎችንም በሚመለከት እነ ዓለም ባንክ ሁሉ ሳይቀሩ የዓለም የፊናንስና ኢኮኖሚ ቀውስ ከመከሰቱ በፊት በዕድገት እንደመነጠቁ ሊያሳምኑን ሞክረው ነበር። ይህ በጥሬ ሀብት ጥያቄና ሽያጭ ላይ የተሰመሰረተ ዕድገት የዓለም ኢኮኖሚ ሲዳከም በዚያው መጠንም ዕድገቱ ወደታች እያለ እንደመጣና ፣ ይህ ዐይነቱ ዕድገት ደግሞ ለምን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊባል እንደማይችል በብዙ ማስረጃ በተደገፈ መልስ ተሰጥቶበታል።

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ፣ የኢህአዴግ አገዛዝ ስልጣን ከያዘና የመዋቅር መስተካከያና(Structural Adjustment Program) የነጻ ገበያ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ እየደጋገመ ሊያሳምነን የሞከረውና የሚሞክረው ፣ አገራችን በከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ እንደምትገኝ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ሰፊው ህዝባችን እየመላለሰ የሚጠይቀው ፣ ይኸው ከአስር ዐመት ጀምሮ የሚደሰኩሩልን ኢኮኖሚው አድጓል እያሉ ነው ፤ ለኛ ግን የሚታየን ነገር ዕድገት ሳይሆን ድህነትና ልመና እንዲሁም ደግሞ አዲስ በናጠጡ የዱርዬ ከበርቴዎች[1] እየተገፋንና በቆሻሻ ቦታዎች እንድንኖር እየተገደድን ነው እያሉ ነው። ስለዚህም ፣ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚባለው ጥቂቱን ማደለብ ፣ ሰፊውን ህዝብ ደግሞ ማራቆት ነው ወይ ? እያሉ ተገቢ ጥያቄ እያቀረቡ ነው። በመሆኑም ፣ ባለን መጠነኛ ዕውቀት ጥያቄዎቻቸውን መመለስ የታሪክ ግዴታችን ሲሆን ፣ በእንደዚህ ዐይነት የገበያ "ኢኮኖሚ ፖሊሲ"[2] አንድ አገር ብሄራዊ ኢኮኖሚዋን መገንባትና ህዝቦቿን ከድህነት ማላቀቅ እንደማትችል ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህም አገራችን

ብሄራዊ ኢኮኖሚ አላት ወይ? የኢኮኖሚ ዕድገትስ ሲባል ምን ማለት ነው የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን ለማቅረብ እንሞክር።

## ለመሆኑ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ኢኮኖሚ አላት ወይ?

በሰባዎቹና በሰማንያዎቹ ዐመታት የደርግ አገዛዝ እንደዚያ በጦርነት ውስጥ ዘፍቆ በሚገኝበት ወቅት አንድ የምዕራብ ጋዜጠኛ የጠየቀው ጥያቄ ለምን ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት አይታይም? እንደዚያ ለጦርነት ብዙ ወጪ እየወጣ ለምንስ ኢኮኖሚው አይከሰከስም? የሚል ተገቢ ጥያቄ ነበር ያቀረበው። ያገኘው መልስ ግን አብዛኛው ህዝብ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ስለሚኖርና ፣ የአንደኛው ኢኮኖሚ ዘርፍ እስከዚህም ድረስ በሌላው ላይ የማይመካ በመሆኑ ፣ አገሪቱ ብሄራዊ ኢኮኖሚ አላት ብሎ መናገር አይቻልም የሚል ነው። ስለዚህም ስለ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ቀውስ መናገር አይቻልም የሚል ነበር መልሱ።

ድሮም ሆነ ዛሬ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ አወቃቀርና የኢኮኖሚ ሁኔታ የተመለከተ ኢኮኖሚው በካፒታሊስት ውስጣዊ ህግና ሎጂክ ላይ ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን፡ አብዛኛው ህዝብ ዘመናዊ ከሚባለው የኢኮኖሚ መስክ ተነጥሎ የሚኖር ነው። ስለዚህም ፣ ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ ቀውስ በምናወራበት ጊዜ ከካፒታሊስት የኢኮኖሚ ዕድገት ሁኔታ ጋር ማወዳደር አንችልም። በሌላ ወገን ግን የካፒታሊስትን ኢኮኖሚ እንደመመዘኛ (Bench Mark) አድርገን በመውሰድ የኢትዮጵያንም ሆነ የብዙ አፍረቃ አገር ኢኮኖሚዎችን አጠቃላይ ዕድገት ማሳየት እንደሚቻል ወይም ደግሞ እንደማይቻል ትንተና መስጠት ይቻላል። ይሁንና ግን ፣ የግዴታ በካፒታሊስት ሎጂክ ላይ ብቻ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ነው ዕውነተኛ ዕድገትን ሊያመጣና የጠቅላላውን ህዝብ ኑሮ ሊያሻሽል የሚችለው ብሎ ይህንን እንደተፈጥሮ ህግ አድርጎ መውሰድ አይቻልም። በመንግስት ጣልቃ ገብነት ፣ በህብረትና በግለሰቦች ተሳትፎ በተቀነባበረ መልክም የአንድን አገር ኢኮኖሚ ማደራጀትና ማሳደግ ይቻላል።

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ከደርግ ጊዜው ይልቅ በተለያዩ መስመሮች የአገራችን ኢኮኖሚ ከግሎባል ኢኮኖሚ ጋር እየተሳሰረ እንዲመጣ በመደረጉ የአብዛኛው ህብረተሰብ ክፍል የኑሮ ሁኔታ በግሎባል ኢኮኖሚ እንዲደነገግ ተደርጓል። 1ኛ)በታሪካችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለት ዓለም አቀፋዊ እህትማማች ድረጅቶች ድንጋጌ የመዋቅር ፖሊሲን መቀበልና ልቅ የገበያን ኢኮኖሚ ተግባራዊ ማድረግ ከግሎባል ኢኮኖሚ ጋር ሊያስተሳስረን በቅቷል። በዚህም መሰረት አገዛዙና ህዝባችን በራሳቸው ህይወትና ምን ዐይነት ኢኮኖሚ ተግባራዊ ማድረግ አለብን ብለው ሊደነግጉ እንዳይችሉ ተደርገዋል። 2ኛ) ከዚህ ጋር ተያይዞ የውስጥን የማቴሪያልም ሆነ የሰውን ኃይል ከማንቀሳቀስ ይልቅ የውጭ „ዕርዳታን“ ተገን በማድረግ ትዕዛዝ ተቀባይ መሆን አገዛዙም ሆነ ህዝባችን አቅመ ቢስ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። አገዛዙ ከምዕራብ መንግስታት በዐመት እስከ ሁለት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚጠጋ ዕርዳታ እንደሚያገኝ ይነገራል። ከአምስት መቶ በላይ የሚጠጉ “ዕርዳታ ሰጪ” ነን ባይ ድርጅቶች በዋና ከተማይቱ ላይ ቢሮአቸውን ከፍተው መንቀሳቀስ በኢኮኖሚው ላይ ፣ በተለይም በምግብ ዋጋና በቤት ኪራይ ላይ ከፍተኛ ጭነት ሊያስከትሉ ችለዋል። 3ኛ) የነጻ ገበያ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን ደግሞ የተወሰነ የህብረተሰብን ክፍል በማደለቡ በህብረተሰብአችን ውስጥ ልዩ የፍጆታ አጠቃቀም ክስተት ሊፈጠር ችሏል። በዚህም ምክንያት ፣ ይህ አዲስ ደልቦ የወጣ የህብረተሰብ ክፍል ተጨማሪ ፍጆታውን ሊያሟላ የሚችለው ከውጭ በውድ ዕቃዎችን እያስገባ ነው። ይህም ማለት በህብረተሰብአችን ውስጥ በአውሮፓ እንኳን የማይታይና ያልተለመደ የፍጆታ አጠቃቀምና ድህነት እዚያው በዚያው እየተጋፉ እንዲኖሩ ተደርጓል። 4ኛ) አዲስ የፍጆታ አጠቃቀም በመለመዱና በዕርዳታ ስም ምን ምን ነገር ውስጣቸው እንዳሉ የማይታወቁ የምግብ ዐይነቶች በገፍ ወደ አገራችን በመግባታቸው ፣ ከዚህ ቀደም በተወሰነው የህብረተሰብ አካባቢ ብቻ ይታዩ የነበሩ በሽታዎችና ሌሎች አዳዲስ የበሽታ ዐይነቶች በመስፋፋት ህዝባችን የዚህ ዐይነቱ የግሎባል ኢኮኖሚ ክስተት ሰለባ ሊሆን በቅቷል። 5ኛ) ለምግብ የሚሆኑ ሰብሎችን ማብቀያ የሚሆኑ ቦታዎች የውጭ ገንዘብ ለመቃረም ሲባል ምርታማ ወዳልሆኑና ለኢኮኖሚ ዕድገትም ድጋፍ ወደ ማይሆኑ የአበባ ተከላና ሌሎች አትክልቶች ላይ በመረባረብ የአገራችን ኢኮኖሚ የግዴታ በውጭ ገበያ ላይ ጥገኛ እንዲሆን ተደርጓል። የአበባን ተከላ ለማስፋፋት ከባንክ ለአምራቾች በብድር መልክ የተሰጠው ገንዘብ ፣ ይህ ምጣኔ ሀብት ለሌሎች ምርታማ ወደሆኑ የምርት ክንውኖች ላይ እንዳይውል አግዶታል። ከዚህም በላይ ፣ ከምንግዜውም በበለጠ ሁኔታ የቡና ተከላንና ገበያን በማስፋፋት አገራችን ከግሎባል ኢኮኖሚ ጋር ዝቅተኛ ምርትን በማምረት የበለጠ እንደትተሳሰርና ፣ የቡና ገበያ ወደ ታችና ወደ ላይ በሚልበት ጊዜ በኢኮኖሚው ላይ

አዎንታዊም ሁነ አሉታዊ ጭነት እንዲያርፍበት ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር ፣ በውጭ ኩባንያዎች አማካይነት ለመኪና ነዳጅ የሚያገለግሉ ሰብሎችን ለመትከል የተሰጠው መሬትና ለምግብ የሚያገለግለው ማሳ ለዚህ እንዲውል መደረጉ የአገራችን ኢኮኖሚ በግሎባል ኢኮኖሚ ተዋንያን መዳፍ ስር እንዲወድቅና ዕድሉ በዚህ እንዲወሰን እየተደረገ ለመሆኑ የአገራችን ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሁኔታ ያረጋግጣል። 6ኛ) ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ወለጆቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ወደ አገር ቤት የሚያስገቡት ዶላር የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ጥገኛ በማድረግ የኑሯቸውን ሁኔታ በየጊዜው በሚላከው ገንዘብ እንዲወሰን ተደርጓል። ይህ ዐይነቱ ጥገኝነትና ከግሎባል ኢኮኖሚ ጋር መተሳሰር ፣እንዲሁም ደግሞ የሁለቱን ዓለም አቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖች ምክር በመቀበል የሞኔተር ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ኢኮኖሚውን አንድ ወጥ ወደ ሆነ ብሄራዊ ኢኮኖሚ እንዲያመራ አላደረገውም። በተቃራኒው ግን ፣ ይህ ዐይነቱ ተቀጥያነት የባሰ ኢኮኖሚውን ዝብርቅርቅና ደካማ ሲያደርገው ፣ በዚያው መጠንም የሀብት መባከንና ድህነት እየተስፋፉ ሊመጡ ችለዋል። ከዚህም ጋር ተደምሮ ፣ የኢትዮጵያ ገበሬ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዝቅተኛ ደሞዝ ተቀጥሮ በመስራት በዓለም አቀፍ ላይ የሚካሄደውን የሀብት ክምች አጋዥ እንዲሆን ተደርጓል። በጥሬ ሀብት አማካይነት ወደ ውጭ የሚፈሰው ሀብት የዚህ የረቀቀ ዓለም አቀፋዊ የሀብት ክምችት ዘዴ ነው።

ይህ ሁሉ ዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ ግፊትና ጣልቃ ገብነት እየተካሄደና ፣ በካፒታሊዝም ሎጂክ ላይ የተመሰረተ የሞነቴሪ ፖሊሲ ተግባራዊ እየሆነ ለምንድነው አገራችን አሁንም ቢሆን አንድ ወጥ ወደ ሆነ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ለማምራት ያልቻለችው? ስለብሄራዊ ኢኮኖሚ ስናወራ በጭንቅላታችን ውስጥ መያዝ ያለብን መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። 1ኛ) ህብረተሰብአዊና የቴክኖሎጂ የስራ ክፍፍል መኖር አለበት። 2ኛ) በተለያዩ መስኮች ዘንድ የስራ ክፍፍል መኖርና መተሳሰር የግዴታ የውስጥ ገበያ እንዲዳብር ያደርጋል። በሌላ አነጋገር ፣ በሰፊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የስራ ክፍፍልና ሰፊ ገበያ መኖር ተደጋጋፊዎች ናቸው። 3ኛ) በባንክ ወይም በክሬዲት መስክና በተቀረው የኢኮኖሚ መስክ መሀከል መተሳሰር ሲፈጠር ፣ የገንዘብ መሽከርከርም ይፈጥናል። ገንዘብ ለፍጆታ የሚያገለግል ብቻ መሆኑ ቀርቶ ወደ መዋዕለ-ነዋይነት ሲለወጥ ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ ዕምርታ ይሰጠዋል። 4ኛ) ለብሄራዊ ኢኮኖሚ መኖር ውድድር(Competition) ዋናው አንቀሳቃሽ ኃይል እንደመሆኑ መጠን ፣ በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ ከበርቴዎች ምርትን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማምረት ሲሉ የግዴታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲተክሉ ይገደዳሉ። ይህ ሁኔታ የግዴታ አዳዲስ የመዋዕለ-ነዋይ መስኮችን መስፋፋትና ጥልቀት ማግኘት ሲያስከትል ፣ ጠቅላላው ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ እያለ ውስጣዊ-ኃይል እያገኘ እንዲመጣ ይገደዳል። 5ኛ) የቴክኖሎጂዎች መስፋፋትና ጥልቀት ማግኘት ደግሞ የውስጥ ገበያን ከማስፋፋትና ከማዳበር አልፎ ፣ ካፒታል ፣ የሰው ኃይልና የጥሬ ሀብት ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ መፍሰሳቸውን አቁመው ወደ ሌሎች ቦታዎችም መሰማራት ይጀምራሉ። ስለሆነም ፣ ከዚህ ጋር ተያይዘው ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችና የከተማ ግንባታዎችና መንደሮች ስርዓት ባለው መልክ በመቆርቆርና በመዳበር ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት መፍጠር ሲቻል ፣ ህብረተሰቡ ወደ መተሳሰር ያመራል። 6ኛ) ለዚህ ዐይነቱ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታና ህብረተሰብአዊ መተሳሰር በምርምር ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ ሁለ-ገብ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ፣ ተጨማሪ ምርትና(Value added) ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት(Social Capital Accumulation) ሊመረትና ሊዳብር የሚችለው በዚህ አማካይነት ብቻ ነው። አንድ ህብረተሰብ ከእጅ ወደ አፍ በሚካሄድ ኢኮኖሚና እዚህና እዚያ ካለ ዕቅድ በሚንቀሳቀስ የኢኮኖሚ ዘርፍ(Informal Sector) እየተመራና እንዲሁም ደግሞ ወደ ውጭ የእርሻም ሆነ ሌሎች የጥሬ ሀብቶችን ሳይፈበረኩ የሚልካቸው ከሆነ ስለ ዕውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ወይም ደግሞ ስለ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ማውራት በፍጹም አይቻልም።

በተለይም የውጭ ንግድን በሚመለከት ፣ የገዢ መደቦቻችንና አማካሪዎቻቸው የሙጥኝ ብለው የያዙት ፈሊጥ አለ። ይኸውም ፣ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የእርሻንና ሌሎች የጥሬ ሀብቶችን እያግበሰበሰች ብትልክ በምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ኢኮኖሚዋን ማሳደግ ይቻላል ከሚል አጉል ዕምነት የተነሳና ፣ በተጨማሪም የፖለቲካ ኢኮኖሚን ህግና የታሪክን ሂደት ግምት ውስጥ ካላስገባ ስሌት በመነሳት ነው። ሰለ አንድ አገር ዕውነተኛ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከአስራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ ምድር ጠለቅ ያለ ምሁራዊ ትግል የተካሄደ ሲሆን ፣ የእርሻ ምርትንም ሆነ ሌላ የጥሬ ሀብትን በጥሬ መልኩ ወደ ውጭ የሚልኩ አገሮች መጥፎን ንግድ(Bad Trade) እንደማካሄድ መቆጠሩ ብቻ ሳይሆን ፣ በጥሬ ሀብት ምርት ላይ የሚሰማሩትም ሆነ ጠቅላላው ህዝብ በምንም ዐይነት ወደ ብልጽግና ማምራትና ብሄራዊ ኢኮኖሚን መገንባት እንዳማይችሉ ነው የተደረሰበት። ከሴራ ፣ እስከ ሚሴልደን ፣ ከዊሊያም ፔቲ እስከ ፍሪድርሽ ሊስትና ካርል ማርክስ እንዲሁም ደግሞ

ሹምፔተር ድረስ ያሉት ታላላቅ የኢኮኖሚክስና የህብረተሰብ ሳይንስ ምሁሮች የሚያረጋግጡት ፤ ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት የጥሬ ሀብት ሳይሆን ዋናው መሰረቱ ፤ በሳይንስ ላይ የተመሰረተ ቴክኖሎጂያዊ እቅስቃሴ ሲሆን ፤ ወደ ውጭ የሚላከው ምርት የግዴታ በፋብሪካ አገር ውስጥ ተፈብርኮና ታሽጎ የተላከ እንደሆን ብቻ በዕርግጥም ዕውነተኛ ሀብትን ማዳበር ይቻላል የሚል ነው። የጥሬ ሀብትንም በየጊዜው በሚፈጠሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በስነ-ስርዓት መጠቀም ይቻላል። በጥሬ ሀብት ብቻ አንድ አገር የምታድግ ቢሆን ኑሮ ፤ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የጥሬ ሀብት ጥያቄና ገበያ ሲጦፍ አብዛኛዎቹ አምራች አገሮች ኢኮኖሚያቸውን ባሳደጉና ከጥገኝነትና ከልመና በተላቀቁ ነበር። እንደ ናይጄሪያና ቬኔዙዌላ የመሳሰሉት ዘይት አምራች አገሮችም ከጥሬ ሀብት አራጋፊነት ተላቀው በዓለም ገበያ ላይ በቴክኖሎጂ ምርት አቅራቢነት ተወዳዳሪ ለመሆን በበቁ ነበር። ወደ አገራችን ስንመጣ የምንገነዘበው ፤ ያልተስተካከለ የንግድ ልውውጥን(Unequal Exchange*) -ያልተስተካከለ ልውውጥ የሚባለው አንድን የፋብሪካ ምርት ለመግዛት ብዙ የጥሬ ሀብት ማምረት ወይም መሸጥ ያስፈለጋል ወይም ደግሞ ብዙ ሰዓት መስራት ያሰፈልጋል ከሚለው የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የመነጨ ነው- የሙጥኝ አድርጎ* በመያዝ ድህነት የባሰ ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ፤ አውቆም ሆነ ሳያወቁ ዕውነተኛውን የብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ መንገድ እንደመዝጋት ይቆጠራል። ከአንድ ዐመት ጀምሮ የሚወራለት የኮሞዲቲ ገበያ ፤ በተለይም ደግሞ ሰሊጥናን ፕሬሚዩም ቡናን ወደ ውጭ ልኮ መወዳደር እንችላለን ፤ ከዚህም ተነስተን የገበሬውን ኑሮ እናሻሽላለን የሚለው መፈክር ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት እንዳይችል የሚደረግ የረቀቀ ሴራ ነው ብል ስህተት አይሆንም። በተጨማሪም ፤ ለገበሬው የኮምፒዩተር ኮርስ እየሰጡ የገበያውን ሂደት እንዲከታተል ማድረግ ይቻላል ፤ በዚህም ይሰለጥናል ማለት የአዲሶቹ የዎል ስትሪት ልጆች ቅዠት ብቻ ነው። በመጀመሪያ ጎጆ ቤት እየኖረ ፤ ኩራዝ እያበራና ንጹህ ውሀንና እንዲሁም ህክምናን ማግኘት ያልቻለ ህዝብ በሌፕቶፕ አማካይነት የዓለምን የገበያ እንቅስቃሴ መከታተል ይችላል ማለት ከፍተኛ ውዥንብር መንዛትና የድህነቱን ዘመን እንደማራዘም የሚቆጠር ነው። ደግሞስ ፤ ለሌፕቶፕ ወይም ለኮምፒዩተር መግዢያ በቂ ገንዘብ ማስፈለጉ ብቻ ሳይሆን ፤ መሳሪያዎችን ለማካሄድ በቂ የኃይል ስርጭት ያስፈልጋል። ያም ሆነ ይህ ፤ ከዚህ ዐይነቱ የጥሬ ሀብት ምርትና ንግድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ፤ ትላልቅ የውስጥ ነጋዴዎችና መንግስት ሲሆኑ ፤ ወደ ውጭ ደግሞ የዓለምን የኮሞዲቴ ገበያ የሚቆጣጠሩት ትላልቅ ኩባንያዎች ብቻ ናቸው። በተለይም የቡና ገበያ በዓለም ኢኮኖሚ ሂደት ላይ ጥገኛ ስለሆነና ብዙ አቅራቢ አገሮችም ስለሚወዳደሩና ገበያውም ከፍና ዝቅ ስለሚል ፤ ዋጋው ዝቅ በሚልበት ጊዜ የግዴታ የገበሬዎችም ገቢ ዝቅ እንዲል ይደረጋል። ከዚህ ስንነሳ በኮሞዲቲ ገበያ ወይም “በተመጣጣጭ ንግድ”(Fair Trade) አማካይነት የሰፊውን የኢትዮጵያ ገበሬ ኑሮ አሻሽላለሁ ማለት ውቅያኖስን በጭልፋ እየጨለፍኩ ድርቅ አደርገዋለሁ እንደማለት የሚቆጠር አነጋገር ነው። በተለይም አሁን በተስፋፋ ”ተመጣጣኝ ንግድ” ወይም ”የተስተካከለ ንግድ” የብዙ የሶስተኛው ዓለም አገር ገበሬዎች ለአውሮፓና ለአሜሪካ ህዝብ ፤ በተለይም ለከፍተኛው የህብረተሰብ ክፍል ጥራት ያለው የእርሻ ምርት እንዲያመርቱ እየተደረገ ነው። ከአርባ በመቶ በላይ የሚሆነው ለአውሮፓና ለአሜሪካ ከበርቴ የሚቀርበው የኦርጋኒክ ምርት የሚመረተው በላቲን አሜሪካና በአፍሪቃ ነው። ይሁንና ከዚህ “ተመጣጣኝ ንግድ” ገበሬዎቹ መጠነኛ ጥቅም ቢያገኙም ከባርነት ስራቸው ግን ሊላቀቁና የተሻለ ኑሮ ሊመሰረቱና ጠቅላለው ኢኮኖሚ ደግሞ በቴክኖሎጂ ላይ እንዲመረኮዝ ሊያደርገው አልቻለም። አይችልምም።

ወደ አገራችን ተመልሰን መሰረታዊ የቲክኖሎጂን ጥያቄ ስንመረመር የኢህአዴግ አገዛዝ የተሳሳተ የሞነቴሪ ፖሊሲ ተግባራዊ ከማድረጉም በላይ አገራችን ዕውነተኛ የኢንዱስትሪ አብዮት ማካሄድ እንዳትችል ብዙ እንቅፋት ተክሎባታል። 1ኛ) የተተከሉት ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ከውጭ እንዳሉ የመጡ ሲሆን ፤ አብዛኛዎቹ ለዕድገት የሚያመቹ አይደሉም። 2ኛ)እንደ ቢሬና ኮካኮላ የመሳሰሉት ፋብሪካዎች በጥሬ ሀብት ከውጭ በሚመጣ የሚመኩ ናቸው። በሌላ አነጋገር ፤ ወደ ውስጥ አገር ቤት ውስጥ ለሚመረቱ ምርቶች እንደገበያ የሚያገለግሉ አይደሉም። በዚህም ምክንያት ፤ ለጥሬ ሀብት ማስመጫ እንደገና የውጭ ምንዛሪ እንዲወጣ ይደረጋል። 3ኛ)በልቅ የነጻ ገበያ ፖሊሲ መሰረት ከትናንሽ ፤ማዕከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ይልቅ የአገልግሎት መስኩ በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ የመጣ ነው። የባንክ ፤ የደህንነት ኩባንያና ስፍር ቁጥር የሌለው የንግድ ክንውን ተስፋፍቷል። የአገልግሎት መስኩ እስከዚህም ከኢንዱስትሪው ጋር በደንብ የተሳሰረ አይደለም። በተጨማሪም ፤ የሁለተኛ ዕቃ(Second Hand) ገበያ በመስፋፋቱ አገሪቱ የአረጁ ልብሶች ፤ማቀዝቀዣዎች ልዩ ልዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችና ካውያዎች እንዲሁም የውሀ ማሞቂያ መሳሪዎች ገበያ በመሆን አውሮፓ ውስጥ ሪሳይክል ሊደረግ የማይችል ወይም የማይፈለግ አገራችን ውስጥ እንዲራገፍ ተደርጓል። በመሆኑም አብዛኛው ህዝብ በዚህ ገበያ የሚመካ እንጂ አዳዲስ የፍጆታ ዕቃዎችን ገዝቶ የመጠቀም ኃይል የለውም።ይህም ማለት

ገበያው ለአዳዲስ ምርቶች ብቃትነት የለውም። 4ኛ)የእርሻ መስኩ ለኢንዱስትሪዎች የጥሬ ሀብት አቅራቢ ሊሆን አልቻለም ፤ ወይም ደግሞ ግኑኝነቱ በጣም የላላ ነው። 5ኛ)የአገሪቱ መጠነኛ ኢንዱስትሪዎች የውድድር ዓለም ውስጥ ነው ያለነው እየተባለ ለውጭ ዕቃዎች ስለተጋለጡ ሊያድጉ አልቻሉም ፤ ወይም ደግሞ እንዲዳከሙ ተደርገዋል። 6ኛ) የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የአገር ውስጥን መለስተኛ ከበርቴዎች በምርት ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚገፋፋ ሳይሆን ፣ እንዲያውም የሚጋፋና በራሱም ካድሬዎች የተቋቋሙት በሰበብ ባስባቡ እንዲነጠቁ የሚያደርግ ነው። 7ኛ)ኢህአዴግ እዚያው በዚያው ነጋዴ ፣ ከበርቴና ተጋፊ እንዲሁም መንግስት እንደመሆኑ መጠን በአገሪቱ ውስጥ ጤናማ ውድድር ማድረግ በፍጹም አይቻልም። ይህም ማለት ፣ በአገዛዙ አማካይነት በአገራችን ውስጥ የዘረፋና ድህነትን የሚያስፋፋ ፣ እንዲሁም ደግሞ ለውጭ ኃይሎች ካለምንም መከላከል የሚያስወርር የኢኮኖሚ ክንውን እየተካሄደ ነው ማለት ነው። ይህ ሁኔታ አምብሮጊዮ ሎሬነዜቲ የተባለው የአስራራተኛው ክፍለ-ዘመን ጣሊያናዊ የሬናሳንስ ምሁር መጥፎ መንግስትና ጥሩ መንግስት(Allegory of Good and Bad Government) በሚለውና በቲያትር መልክ ባቀረበው ትዕይንቱ ፣ መጥፎ መንግስት በዘራፊነት ፣ ሴትን አስገድዶ በመድፈር ፣አገርን በማፍረስና በግድያ የሚገለጽ ሲሆን ፣ ጥሩ መንግስት ደግሞ ቆንጆ ህንፃዎችን በመስራት ፣ የሚያማምሩ ሱቆች እንዲከፈቱና ንግድ እንዲዳብርና ፣ በዚህም መሰረት ጠቅላላው ህብረተሰብ በደስታ ዓለም ውስጥ እንዲኖር የሚያደርግ ነው የሚለውን ዐይነት የሚገልጽ ነው በኢህአዴግ መንግስት በአገራችን ምድር ተግባራዊ ሲሆን የከረመውና አሁንም የሚካሄደው። በዚህም ምክንያት ፣ ወጣቱ ፈጣሪ ከመሆን ይልቅ አንዳንዱ ወደ ብልግና ኢንዱስትሪ ውስጥ ሲሰማራና ጫአት ቃሚ እንዲሆን ሲፈረድበት ፣ ዕድል ያገኘው ደግሞ በዚህም በዚያም ብሎ አገሩን ለቆ እንዲሰደድ እየተደረገ ነው። በተበላሸ  የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተነሳም ክትፎ ቤቶች ጫአት መነገድ ያዋጣል እየተባለ ወደ ጫአት መቃሚያነት ቦታዎች እየተለወጡ ነው። በዚህ መልክ ደግሞ ህብረተሰብአዊ ሀብት የሚፈጠር ሳይሆን ፣ የሰው ተፈጥሮአዊ ዕውቀትና ሀብት እንዲፈርስ በማድረግ ጠቅላላው ህዝብ አቅመ-ቢስ እንዲሆን ተደርጓል። ከዚህ በተረፈ ፣ ካለብዙ ጥናት እዚህና እዚያ የሚተከሉት ኢንዱስትሪዎች የአካባቢን ስታንደርድ ያልጠበቁ በመሆናቸው ፣ በአካባቢና በሰው ጤንነት ላይ ከፍተኛ መዛባትና መቃወስ እያስከተሉ ነው።

ስለኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ የግዴታ የአንድ አገር ኢኮኖሚ በካፒታሊስታዊ ሎጂክ ላይ መመርኮዝ አለበት የሚል ህግ የለም። በተለይም እንደኛ ያሉ የተዝረከረከ ኢኮኖሚ ያላቸው አገሮች የግዴታ በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስፈልጋቸዋል። በዚህም ምክንያት በታሪክ ውስጥ በመጀመሪያው ወቅት የብዙ አገር ኢኮኖሚዎች በመንግስት የዕውቅ ፖለሲ መልክ ነው ሊይዙና ቀስ በቀስ ሊፍታቱ የቻሉት። ሌሎች አስተሳሰቦችን ወደ ጎን ትተን ፣ ሌላው ቢቀር እንኳ የጀርመን ናዚዎች በሰላሳኛው ክፍለ ዘመን የቨርሳይል ማዕቀብና ክፍያ የጣለባቸውን ከቁጥር ውስጥ ሳያስገቡ በ13 የግዛት ዘመናቸው ብዙ ከተማዎችንና ኢንዱስትሪዎችን እንዲሁም ትላልቅ መንገዶችን ሰርተዋል። በጊዜው የሂትለር አገዛዝ ከዓለም የገንዘብ ገበያ ላይ ብድር ማግኘት አይችልም ነበር። በአንፃሩ ግን ጀርመን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ላደረገችው ጥፋት ካሳ መክፈል ነበረባት። በተጨማሪም ፣ ራሽያ በኋላ ደግሞ የሶቭየት ህብረት የአንደኛ ዓለም ጦርነት ያደረሰባትን ግፍና ኢኮኖሚያዊ መከስከስ ተቋቁማ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ ባጭር ጊዜ ውስጥ የቴክኖሎጂ ምጥቀት ልታሳይና አቶም ቦንብን ለትሰራ ችላለች። እዚህ ላይ እነዚህ ሁለት አጥፊ ኃይሎች በህዝቦቻቸው ላይ ያደረሱትን ግፍ ሳንዘነጋ ፣ በኢኮኖሚ ፖሊሲ በኩል ከዚህ አልፈው ሊሄዱ የሚችሉ አልነበሩም። በሌላ አነጋገር ፣ ከኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ አገራቸውን ትልቅ እናደርጋለን ከሚለው አስተሳሰብ አኳያ ሁለቱም አምባገነን ኃይሎች ከብዙ የአፍሪቃ መሪዎች ይሻላሉ ብል አልሳሳትም። ይህ ማለት ግን ግፋቸው ይደገፋል ማለት ሳይሆን ፣ እኛ ጥቁሮች በድርጅትና አገርን በመገንባት ረገድ ያለን ኃይል ከቁጥር ሊገባ አይችልም ለማለት ብቻ ነው። አሁንም ለማስመር ፣ ከሰብአዊነት አንፃር በህዝብ ላይ ያደረጉት ድርጊት በፍጹም ተቀባይነት የለውም።

ከዚህ ስነንሳ አደገ እየተባለ ብዙ የሚለፈፍበት የአገራችን ኢኮኖሚ መስረታዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግን ያልተከተለ ብቻ ሳይሆን ፣ በተጨማሪም በቀላሉ ልንወጣው የማንችለው ማህበረሰብአዊና የአካባቢ ቀውስ ውስጥ የከተተን ነው። ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚባለው የቁጥር መጨመር ወይም የዐይነት ለውጥ መሆኑን ተቀባይነት ካገኘው ስሌት ዐመታዊ የአገር ውስጥ ምርትና አገልግሎት አንፃር ጠጋ ብለን እንመርምር።

# የምርት በቁጥር መጨመር ወይስ ዐይነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት!

የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች የበላይነትን ከተቀዳጁና በየትምህርት ቤቱ ይህንን መሰረት ያደረገ ትምህርት በመሰጠቱ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት የተዛባ አስተሳሰብ እንዲስፋፋ ተደርጓል። አብዛኛውን ጊዜ ስለኢኮኖሚ ዕድገት ሲወራም ተማሪዎች የአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት ከምርትና ከአገልግሎት በቁጥር ከመጨመር በስተቀር አልፈው እንዳያስቡ በመደረጋቸው በኢኮኖሚ ዘርፎች መሀከል ሊኖር የሚችለውን መተሳሰር ጠጋ ብለው እንዳያዩ ተጋርደዋል። በተጨማሪም ፣ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እያደገ የመጣው የብሄራዊ ኢኮኖሚ በተወሰነ ቦታና ሰዓት ብቻ የሚለካ መሆኑ ቀርቶ ፣ የተወሰኑ ኢንስቲቱሽናዊ ቅድመ-ሁኔታዎች ከተሟሉ ሰፋ ባለ መልክ የሚካሄድና ባለው ውስጠ-ኃይል ሰፋ ያለ ቦታን የሚያዳርስና የጊዜን አጠቃቀም ጉዳይ በቁጥር ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ ግልጽ በሆነ መልክ አይቀርብም። ስለዚህም ፣ ተራ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተሳሰብ ብዙ ሰዎችን እያሳሳተ ነው። በተጨማሪም በሬናሳንስ ዕውቀት የሰለጠኑ ኢኮኖሚስቶች ኢኮኖሚ ዕድገትን ለኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ብለው ግምት ውስጥ ያስገቡ ሳይሆን ፣ ዋናው የኢኮኖሚ ዕድገት ፍልስፍናዊ አስተሳሰብ የሰውን ልጅ ሚና የሚያስቀድምና የመፍጠር ኃይሉንም ከፍ በማድረግ ማቴሪያላዊ ሁኔታዎችን ከመንፈስ ተሀድሶና ደስታ ጋራ በማዋሃድ በመተሳሰብ እንዲኖር የሚያደርግ ነው። በተለይም ለጥበብ ከፍተኛ ቦታን በመስጠት ፣ ምርትም ሆነ የሰው ልጅ አኗኗር የተወሰነ ህግና ስርዓትን እንዲሁም ደግም ውስጣዊ ስምምነትን(Order and Harmony) በመያዝ ህብረተሰብአዊ ስርዓት እንዲመሰረት ማድረግ ነው። ይህንን እየተቃረነ የወጣው የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚክ ፍልስፍና ግን የሰው ልጅ በአፈጣጠሩ ስግብግብና የራሱን ጥቅም አሳዳጅና አስቀዳሚ(Utilitarian Thinking) ነው እያለ በማስተማሩ ፣ ምርትን በቁጥር መጨመር እንደዋናው መሰረተ ሃሳብ አድርጎ በማቅረብ የብዙ ሰዎች አስተሳሰብ እንዲዛነፍ አድርጓል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ተዝረክረከውና ተሰደው እንዲኖሩ ተገደዋል። ያላቸውን የመፍጠር ችሎታ እየተጠቀሙ ሀብትን እንዳያፈሩ ተገደዋል። በዘመናዊ ሰባኪዎችና ተዋናዮች በቀላሉ ሊወናበዱ በቅተዋል። ይሁንና ግን ፣ የትምህርት ቤት ኢኮኖሚክስን የምርትና አገልግሎት ስሌት እየዘረዘርን ስንመለከት ደግሞ ከራሱ መሰረታዊ አስተሳሰቦችን ማውጣት እንችላለን።

በአጭሩ ስለኢኮኖሚ ዕድገት ወይም በቁጥር መጨመር ስናወራ ፣በአንድ አገር ውስጥ የሚካሄድ ኢኮኖሚያዊ የምርትና የአገልግሎት ክንውን ካለፈው ዐመት ጋር ሲወዳደር መብለጡን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ $ሀ_1 > ሀ_0$ ፤ ሀ በአንድ አገር ውስጥ የሚመረተውን ጠቅላላ ምርት የሚያሳይ ስሆን ፣ በዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት ጊዜ ውስጥ የህዝብም ቁጥር በዚያው መጠን ካደገ ኢኮኖሚው አላደገም ማለት ነው። ከዚህ ጭንቀት ለመውጣት የኢኮኖሚው ዕድገት በመቶ ሲለካ ይህን ያህል ማደጉን ግምት ውስጥ ከማስገባት ይልቅ ፣ ስለኢኮኖሚ ዕድገት የተሻለ ስዕል የሚሰጠን ፣ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ ራሱን ለማስተዳዳር ወይም ለማሸነፍ ሲል በነፍስ ወከፍ የሚያገኘው ዐመታዊ ገቢ ከፍተኛ ግምት ውስጥ የገባ እንደሆነ ነው። የአንድ ሰው ዐመታዊ የነፍስ ወከፍ ደግሞ ሊገመት የሚችለው ኢኮኖሚው ይህን ያህል በቁጥር ጨምሯል ስለተባለ ሳይሆን ፣ የየግለሰቡ ምርታማነት(productivity) ግምት ውስጥ የገባ እንደሆን ነው። የምርት ዕድገት ምርታማነት ደግሞ በቴክኖሎጂ ዐይነትና በሰው ዕውቀት የሚለካ ነው። በሌላ አነጋገር ፣ ሰለ ኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ ከቴክኖሎጂ ዕድገት አጠቃቀምና በምርት ክንውን ውስጥ የሚሳተፍ ግለሰብ በተወሰነ ሰዐት ውስጥ በራስ ወከፍ ሲለካ ይህንን ያህል ማመረት ይችላል ከተባለና ፣ የሚደርሰውም ድርሻ ራሱንና ቤተሰቡን ሊያስተዳደርበት ይችላል ከተባለ ፣ ዕውነትም ኢኮኖሚው በቁጥር ብቻ ሳይሆን በዐይነትም አድጓል ማለት ይቻላል።

ለምሳሌ በአንድ አገር ውስጥ የሚመረተውን አጠቃላይ ምርትና በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሳተፉተን የኢኮኖሚ ኤጀንትስ ስንመለከት ፣ በአንድ በኩል ገንዘባቸውን በምርት ክንውን ውስጥ የሚያፈሱ አሉ ፤ በሌላ ወገን ደግሞ በፋብሪካ ውስጥና በእርሻ መስክ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ አሉ። ይህ ዐይነቱ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ከውጭ የሚመጣውንና በምርት ክንውን ውስጥ የሚገባውን ከቁጥር ውስጥ የሚያስገባ አይደለም። ስለዚህም ፣ በአንድ የተዘጋ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚመረት ምርት በዚያው መጠንም በአምራቹ ተግዝቶ ለጥቅም የሚውል መሆን አለበት። እንደሚታወቀው ፣ ማንኛው ገንዘብ ያለው ከበርቴ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚሳተፈው ፣ የሚያመርተውን ገበያ ላይ አውጥቶ ለመሸጥና ትርፍ ማግኘት የቻለ እንደሆን ብቻ ነው። የትርፉ መጠን ደግሞ የቱን ያህል ለመስፋፋትና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ገዝቶ በምርት ክንውን ውስጥ እንዲካፈልና እንዲወዳደር ይረዳዋል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ፣ የምርት ክንውን ተከታታይነት እንዲኖረውና ዕድገትም

እንዲያሳይ ከተፈለገ የግዴታ በየጊዜው ጥራት ወዳለው ቴክኖሎጂ መሸጋገር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በዚያው በአገር ውስጥ የተሻለን ቴክኖሎጂ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሌሎች ከበርቴዎች መኖር አለባቸው። ለፍጆታ የሚውልን ምርት በሚያመርቱ ከበርቴዎችና መሳሪዎችን እየሰሩ በሚያቀርቡ መሀከል የጠበቀ ግኑኝነት መኖር አለበት ማለት ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ በፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ ራሱ ያመረተውን ምርት ገዝቶ ሊጠቀም እንዲችል ከስራ ጉልበቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተጨባጭ ደሞዝ(Real Income) ማግኘት አለበት። በዚህ መልክ የሚንቀሳቀስ ኢኮኖሚ በአምስት መሰረታዊ ሃሳቦች የሚደገፍ ነው። 1ኛ) በዐመት የሚያድገው የህዝብ ቁጥር ፣ 2ኛ) በጠቅላለው ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈጠረው የሀብት ክምችት(Physical Capital Accumulation) 3ኛ) የመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴና ከዚህ ጋር የሚጓዝ የቴክኖሎጂ ምጥቀት ለኢኮኖሚው ዕድገት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። 4ኛ) በህብረተሰብ ውስጥ ያለው የዕውቀት ዐይነትና የህዝቡ የፈጠራ ችሎታ ፣ 5ኛ) ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመቹ ዲሞክራሲያዊ ኢንስቲቱሽኖች መኖር ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። እነዚህ መሰረተ ጉዳዮች ወይም ቅድመ-ሁኔታዎች በሌሉበት አገር ስለኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት በፍጹም አይቻልም። ምክንያቱም የጠቅላለው የአንድ አገር ህዝብ ዐመታዊ ገቢ ሊወሰን የሚችለው ሰፋ ያለ መዋዕለ-ነዋይ ሲካሄድ ብቻ ነው። ሰፋ ያለ የመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴ ከተካሄደ ደግሞ የስራ መስኮች ይከፈታሉ። ከስራ መስክ መከፈት ጋር የሰራተኛው የወር ወይም የዐመት ገቢ እያደገ ሲሄድ የመግዛትና የመቆጠብ ኃይሉም ይጨምራል። ይህ አጠቃላይ ስዕል በጠቅላለው በኢኮኖሚው ውስጥ የሚሳተፉትን ኃይሎችና መስኮች እንዲተሳሰሩና እንዲደጋገፉ ያደርጋቸዋል። ከዚህ ስንነሳ በትምህርት ቤት በፎርሙላ መልክ የሚሰጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ትምህርት ዘርዘር ብለን ስንመረምረው እንዲያው የምርት የቁጥር መጨመር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዐይነት ወይም የጥራት ለውጥም እንዳለ መገንዘብ ይቻላል ማለት ነው።

እንደሚታወቀው የአንድ አገር ኢኮኖሚ በፋብሪካ ፣ በእርሻና በአገልግሎት መስክ በደሞዝ ተቀጥረው በሚሰሩትንና በአሰሪዎች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ፣ መንግስት በአንድ በኩል ከህዝብ የቀረጥ ገቢ ያገኛል ፤ በዚህም በሰራተኛውና በአሰሪው ኪስ ውስጥ የሚቀረውን ገንዘብ ይወስናል። በሌላ ወገን ደግሞ በሚያገኘው ገቢ ራሱ ጠያቂ በመሆንና በተለያዩ ህዝብን በሚጠቅሙ የአገልግሎት መስጫ መስኮች ላይ ኢንቬስት በማድረግ በጠቅላለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። በተጨማሪም የአንድ አገር ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከውጭ ጋር ባለው ግኑኝነት ይወሰናል። የማምረቻ መሳሪያዎች ፣ በግማሽ መልክ የተፈበረኩ የጥሬ ሀብቶችና የፍጆታ ዕቃዎች በመግባት ለኢኮኖሚው ልዩ ገጽታ ይሰጡታል። ይሁንና ግን እነዚህ ከውጭ የሚመጡ የጥሬ ሀብቶችና የማምረቻ መሳሪያዎች አገር ውስጥ እንደተመረቱ ተደርገው መታየት የለባቸውም። ይህ ከሆነ የኢኮኖሚው ዕድገት ሌላ መልክ ይይዛል ማለት ነው።

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ስሌት በደንብ ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባትና አንድ ምርት በድጋሚ ስሌት ውስጥ እንዳይገባ በአንድ በኩል ከውጭ እንደ ጥሬ ሀብት የገባውንና በምርት ሂደት ውስጥ የተሳተፈውን መቀነስ ሲያስፈልግ ፣ በሌላ ወገን ደግም እዚያው አገር ውስጥ የሚመረተውን ምርት ደረጃ በደረጃ የመጨረሻውን ምርት ወይም ተጨማሪ ምርት (Value added) ብቻ በማስላት በቁጥር የሚለካውን የዕድገት ሁኔታ መወሰን ይቻላል። ለምሳሌ አንድ ዳቦ ጋጋሪ ተጨማሪ ምርት ማምረቱን ለማስላት የግዴታ የገዛውን ዱቄትና እርሾ መቀነስ አለበት። ተደራራቢ ስሌት እንዳይኖር የግዴታ በየኢኮኖሚ ክንውን ሂደት ውስጥ ከውጭ የመጡትን መቀነስ ስለጠቅላላው ኢኮኖሚ ማደግና አለማደግ አጠቃላይ ስዕል ሊሰጠን ይችላል ማለት ነው።

ይሁንና ግን ፣ በኒዎ-ሊበራሊዝም የተደረሰበት የኢኮኖሚ ዕድገት ስሌት በአንድ የኢኮኖሚ ውስጠ-ኃይል(Dynamism) ውስጥ ያለን መሰረታዊ ጉዳይ ጠጋ ብለን እንዳናይና እንዳንመረምር ሊጋርደን ይችላል። ለምሳሌ በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ፣ አገራችንንም ጨምሮ ከቁጥር ውስጥ የማይገባና ብዙም ደንታ የማይሰጠው ጥበባዊ የከተማና የመንደሮች አገነባብ አለ። በሌላ አነጋገር ፣ የከተማዎችና የመንደሮች አመሰራረትና አገነባብ ከኢኮኖሚ ዕድገት ተነጥሎ ሊታይ በፍጹም አይችልም። ከዚህም በላይ ፣ ንጹህ ውሀን በየቤቱ በቧንባ ማቅረብና በየጊዜው ጥራቱ መጠበቁን መከታተል ፣ ለመቀቀያና ለመብራት የሚውል የኃይል ማመንጫ ጉዳይ ፣ የመጸዳጃና የካናል ስይስተም ፣ እነዚህ ሁሉ ከኢኮኖሚ ዕድገት ተነጥለው ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም። ምክንያቱም አንድ ህዝብ የሚኖረው ሆዱን ለመሙላት ብቻ ስላልሆነ ከፍጆታ ዕቃዎች ባሻገር ከላይ የተጠቀሱትም ነገሮች መሟላት በእርግጥም ራሱንና አካባቢውን ለመለውጥ የሚችል ፍጡር መሆኑን ያረጋግጡለታል። ስለዚህም ፣ በኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችም መካተት አለባቸው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፣ ስትራቴጂክ የሚባሉና በኢኮኖሚ

ዕድገት ስሌት ውስጥ የማይታሰቡ አሉ። ለምሳሌ እንደ እሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያዎችና መኪናዎች ፣ የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ቶሎ ብሎ ህዝብን ለማዳን የሚያስችል መሳሪዎች ወይም የቴክኒካል ዕርዳታዎች... ወዘተ. እነዚህ ሁሉ በኢኮኖሚ ግንባታና ዕድገት ውስጥ መካተት ያለባቸው ናቸው። ከዚህ ውጭ ህብረተሰቡን እንደ ህብረተሰብ የሚይዙትና ራሱንም እንዲያውቅ የሚያደርጉት የቲያትር ፣ የሙዘዬምና ሌሎች ይህንን የመሳሰሉና የሰፊውን ህዝብ መንፈስ የሚያድሱ ከኢኮኖሚው ዕድገትና ግንባታ ጋር ተያይዘው መሄድ ያለባቸው ናቸው። ከዚህ ሰፊና ግን ደግሞ አጠር ባለ መልክ በቀረበው በመነሳት ነው የኢህአዴግን የአስር በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት መገምገም ያለብን። በተያያዘም ፣ የኒዎ-ሊበራሊዝምን አፍራሽና በንጹህ የፍጆታ አጠቃቀም ላይ የተመሰረትን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንነት መረዳት የሚቻለው።

ከዚህ ስንነሳ በኢህአዴግ የአስራ ዘጠኝ የግዛት ዘመን አገሪቱን አንድ እርምጃ ወደ ፊት የሚያራምዱ ምን ያህል ስትራቴጂክ ኢንቬስትሜንቶች ተካሄዱ? በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ዘንድስ የቱን ያህል ግኑኝነት ተፈጠረ? የስራ ክፍፍሉስ የቱን ያህል ሊዳብር ቻለ? ለስንት ሚሊዮን ህዝብስ የሚሆን የስራ መስክ ተከፈተ? ስንት መንደሮችና ከተማዎችስ ተቆረቆሩ ፣ተገነቡ? ባጭሩ ህዝባችን ከልመናና ከድህነት እንዲሁም ከተደጋጋሚ ረሀብ የሚያላቅቁትና ኩራተኛ ዜጋ የማያደርጉትት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አስራ ዘጠኝ ዐመታት ተካሄደዋል ወይ? ባለን የዜግነት ኃላፊነትና እንደማንኛውም ማቴሪላያዊና መፈንሳዊ ፍላጎት እንዳለው የሰው ልጅ ሁሉ ፣ ለክቡር ጠቅላይ ሚንስተራችንና ለክቡር ፕሬዚደንታችን የምናቀርብላቸው ጥያቄዎች ፣ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ የኢኮኖሚ ተቋሞችን አሟልታችኋል ወይ? በየዐመቱ በቁጥር ኢኮኖሚው በዚህ መጠን አድጓል ከማለት ባሻገር ፣ በዐይናችን የምናየው ፣ በእጃችን የምንዳስሰውና የምንቀምሰውና የምንልሰው ብቻ ሳይሆን ፣ ስናይም የምንደሰትበትን የኢኮኖሚ ዕድገት አሳይታችኋል ወይ? ብለን ነው የምንጠይቃቻው። በአጭሩ የእናንተ በቁጥር የሚለካ ዕድገት ታሪክ ሊያሰራ የሚችል ነው ወይ ? ለብሄራዊ ኢኮኖሚ መሰረት የጣለና ተከታዩ ትውልድ ደግሞ በሱ ላይ ተመርኩዞ የሚሻሻለውን እያሻሻለና እያረመ ለመገንባት የሚያስችለው መሰረት ጥላችሁልናል ወይ? ብለን ነው በክብር የምንጠይቃቸው። ካለበሊዘያ የምታወሩልን ሁሉ ነገር በቅዠት ዓለም ውስጥ እንድንኖር የሚያደርገንና ፣ ብንን ስንል ለካን ቃዠተን ነበር ፣ በውን የምናየው ግን ልመናና ድህነት ፣ ቆሻሻና ግማት ፣ አቅድ የሌለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ውርውር እንደሆነ ነው እያልን ነው ራሳችንን ይዘን የምንጮኸው። እናንተ የኢኮኖሚ ዕድገት የምትሉን በጥቂት ሰዎች ጭንቅላት ውስጥ የሚብላላውን ፣ ጥቂት ሰዎችን ያደለበና አገርን የሚያዘርፍና የሚያፈራርስ ከሆነ ስለኢኮኖሚ ዕድገት አይደለም የምታወሩልን። ከእናንተና ከጥቂት በአየር ላይ የሚንሳፈፉ የሚመስሉ ሰዎች የማያልፍ የኢኮኖሚ ዕደገት መሰረት የሌለው ብቻ ሳይሆን ፣ ዛሬ እንደምናየው ፣ የዓለም ህዝብ ሆይ! ህዝባችን ተርቧልና ድረስልን ከሚያስብል የማያልፍና አሳፋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ስሌት ነው የምታወሩልን ነው የምንላችሁ። አሁንም ፈለሳፋው እንዳለው ፣ ተጨባጩ ሁኔታ ምንድነው የሚነግርህ? ጥሩ ወይስ መጥፎ ነገር! የኤክስፐርቶችም ኤክስፐርትነትም የሚረጋገጠው በኢኮኖሚትሪክስ በተሰላ የኢኮኖሚ ዕድገት ሳይሆን ፣ በግለሰቦች ሆነ በአንድ ህዝብ ላይ የሚታየው የኑሮ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ግንዛቤ ውስጥ የገባ እንደሆን ነው።

በአሀዝ የሚገለጸውን ኢኮኖሚ ዕድገት ለመረዳት ከተራ ሎጂክ አንፃር ተነስተን ሁኔታውን እንመርምር። ክቡር ፕሬዚደንታችን በፓርላሜንት የመክፈቻ ንግግራቸው ላይ የውስጥና የውጭ ችግር ተደቅኖብንም ኢኮኖሚያችንን ማሳደግ ችለናል ብለዋል። ችግር ያሉትን ግን አላብራሩም። ይሁንና ግን ፣ እኛ የምናውቀው የአገር ቤት ውስጥ ችግር በምንዛሪ እጥረት የተነሳ ከውጭ ለፋብሪካ የሚሆኑ የጥሬ ሀብት ማስገባት እንዳልተቻለና በዚህም ምክንያት ብዙ ፋብሪካዎች ስራቸውን እንዳቀዘቀዙ ነው። በተጨማሪም ፣ ሲሚንቶ ከመወደዱ የተነሳ ወይም ደግሞ እንደልብ ስለ ማይገኝ ብዙ ህንፃዎች ተጀምረው ቆመው እንደቀሩ ይነገራል። ይህ ማለት ፣ በፋብሪካዎችና በተወሰነው የአገልግሎት መስክ ዘንድ የምርት ክንውን በከፍተኛ ደረጃ መቀዝቀዝ ይታያል። ይህም ማለት ፣ ኢኮኖሚው ችግር ውስጥ ይገኛል ማለት ነው። ከዚህም ስንነሳና ከምርት ክንውን መቀዝቀዝ ጋር የገቢንም ሁኔታና መቀነስ ስናካትት ፣ እንደሚወራው ኢኮኖሚው አድጓል ብለው መሪዎቻችን ሊያሳምኑን አይችሉም። ወደ እርሻ መስኩም ስንሄድ የዝናብ እጥረት እንዳለና በዚህም ምክንያት የምርቱ ሁኔታ አስተማማኝ እንዳልሆነ ይነገራል። በተጨማሪም ፣ በመሬት ጥበትና ወደ ኋላ በቀረ ቴክኖሎጂ ምክንያት የገበሬው የማረስ ኃይልና የመሬቱ ምርታማነት በየዐመቱ እየቀነሰ እንደመጣ መገንዘብ ይቻላል። ምናልባት ተስፋፉ የሚባሉ የቡናና የአበባ ተከላ ፣ እንዲሁም ደግሞ ለመኪና ነዳጅ የሚያገለግሉ አትክልቶች ኀላ ብለው የሚታዩና በስሌት ውስጥ የሚገቡ ከሆነ ጠቅላለውን ኢኮኖሚ በቁጥር ከፍ ሊያደርጉት ይችላሉ። የአልግሎት መስኩንም ስንመለከት ፣ በተለይም ተጧጡፎ የሚገኘውን የሆቴልና ትላልቅ

ህንፃዎች ስራ ቁጥር ውስጥ ስናስገባ ምናልባትም የኢኮኖሚውን ዕድገት ሊተኩሰው ይችላል ማለት ነው። ይህ ማለት ግን ከፊዚካል ኢኮኖሚክስ ስሌት አንጻርና ላይ ከገልጽኩት ሁኔታ ስንነሳ ኢኮኖሚው አድጓል የሚያስብል አንድም ማረጋገጫ የለም። በሌላ ወገን ፣ አንዳንድ ኢህአዴግን የሚደግፉ ኢኮኖሚስቶች ሊያሳምኑን የሚሞክሩት የዋጋ ግሽበት መኖር የኢኮኖሚው ዕድገት ነጸብራቅ ነው የሚለው በሳይንስ የሚረጋገጥ አይደለም። እንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ በስድሳዎች ዐመታት በብዙ የካፒታሊስት አገር ኢኮኖሚዎች ዕድገት ጋር ተያይዞ የጥሬ ሀብት ጥያቄና ክሬዲት ያደገበት ዘመን በወድድር ምክንያት የተነሳ የማምረቻ ዋጋ ሲጨምር(Cost-push) ፣ የግዴታ አጠቃላይ የዋጋ ግሽብትም ሊታይ ችሏል። ይህንን የመሰለውን ውስጠ-ኃይሉ ከፍተኛ የሆነውን የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕድገትና የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በፍጹም ማወዳደር አይቻልም። ሁለቱም ኢኮኖሚዎች በተለያዩ ህጎች የሚተዳደሩ ናቸው።

ያም ሆነ ይህ ፣ አጠቃላይ የአገሪቱ ስዕል የሚሰጠን ማስረጃ ኢኮኖሚው በዚህ መጠን አድጓል እያልን እንድንዝናና የሚያደርገን አይደለም። 1ኛ)ፕሮፌሰር ኃይለማርያም በሳምንታዊው የሰኞ ጽሁፋ ላይ በጣም ጥሩ አድርጎ ባቀረበው መሰረት ፣ እንደ ጅማ ባሉ ሀኪም ቤቶች አስፈላጊው የህክምና መሳሪዎች አለመኖራቸው ብቻ ሳይሆን ፣ የሆስፒታሉ መቆሸሽ እጅግ የሚዘገንና የሚያሳፍር ሁኔታ ውስጥ እንዳለን የሚያረጋግጥ ነው። 2ኛ)እዚህ አገር ያደገችና በቁንጅና ውድድር ያሸነፈችው ሳራ በቅርቡ ኢሊባቦር ትምህርት ቤት ለማሰራት ሄዳ አካባቢውንና የህዝቡን ሁኔታ እንዲሁም ደግሞ የሆስፒታሉን ሁኔታ መቆሸሽ አይታ ስታልቅስ የተነሳቸውን ቪዲዮ የተመለከተ ሰው አገራችን በምን ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለች መሪዎቻችንና ስታትስቲክስ ከሚሰጡን የተሻለ ስዕል ማግኘት እንችላለን። አሁን በቅርብ ማስትሬቷን እዚህ አውሮፓ ለመስራት የመጣችና ብዙ ዐመታት ገጠር ውስጥ የሰራች ኢትዮጵያዊት እንዳጫወተችኝ ከሆነ ፣ በአዲስ አበባና በተቀረው የክፍለ ሀገር ከተሞችና እንዲሁም ገጠሮች መሀከል በሚኖረው ህዝብ ዘንድ ያለው አስተሳሰብና የአኗኗር ሁኔታ የሰማይና የመሬትን ያህል ርቀት እንዳለ ነው። በሌላ አነጋገር ፣ አብዛኛው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አዲስ አበባና አካባቢው የሚካሄድ ነው ማለት ነው። 3ኛ) በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ገጠሮችና መንደሮች በደንብ የተዘጋጀ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባለመኖሩ ፣ በተለይም ዕድሜያቸው የገፋና ደጋፊ የሌላቸው በችግር ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ። አንድ ሽማግሌዎችን የሚረዳ የተራድዖ ድርጅት(Helpage) ባደረገው ጥናት ብዙ እናቶችና አባቶች በድብቅ ረሀብ እንደሚሰቃዩ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፣ ፓን አፍሪቃን የነፃነትና የፍትህ ድርጀት የሚባለው ሰራተኞቹን ኢትዮጵያ ልኮ ባደረገው ጥናት ፣ አዲስ አበባ ውስጥም ሰፊ ችግር እንዳለና በደሀውና በአዲሱ ሀብታም መሀከል ያለው ልዩነት መረን የለቀቀ መሆኑን ያስረዳል። በጥናቱ መሰረት ፣ አሁን ተከሰተ የተባለው ረሀብ ቀደም ብሎ የታወቀ ሲሆን ፣ መንግስት ወደ ውጭ እንዳይወጣ አፍኖት ይዞት እንደነበር ያስረዳል። በተለይም ራሳቸውን ለማሸነፍ ሲሉ ብዙ ወጣት ሴቶች በሴተኛ አዳሪነት እንደሚተዳደሩና በየመንገዱ እንደሚቀዋለሉ ድርጅቱ በጥናቱ ገልጿል። 4ኛ)ህጻናትና ወጣቶች የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ለተመለከተ ሰው ፣ በማደስ ችግር ወይም ትምህርት ቤቶቹ አቅድ ባለው መልክ ባለመሰራታቸው የተነሳ እንደፈራረሱና የህጻናቱንም የልብስ ሁኔታ ለተመለከተ ስለ ኢኮኖሚ አድጓል አላደገም እያልን የሚያጨቃጭቀን ምክንያት የለም። 4ኛ)በንጽህና ጉድለት ፣ ተጨናንቆ በመኖርና በቂ መጸዳጃ ባለመኖርና ንጹህ ውሀ ባለማግኘትና ከሰውነት ኃይል መዳከም ጋር ተደምሮ በቅርቡ ብዙ ሰዎች በኮሌራ በሽታ እንደሞቱ ይታወቃል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፣ በአንዳንድ ከተማዎች የተስቦና የጆሮ ደግፍ በሽታ መስፋፋትና ፣ ብዙ ሰዎችም ለሞት መዳረግ የአገራችን ኢኮኖሚ በምን ዐይነት ሁኔታ እንደሚገኝና አገዛዙም እነዚህን መሰረታዊ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ማሟላት እንዳልቻለ ነው የሚያረጋግጥልን። 5ኛ)በየሀኪም ቤቶች ፣ የሀኪሞች ፣ የነርሶችና የድሬሰሮች እጥረት የተነሳ በቁጥር እየጨመረ የመጣውን ታማሚ ህዝብ ለማከም የማይቻልበት ሁኔታ ተደርሷል። በተጨማሪም ፣ እንደ ጅማ ባሉ ከተማዎች አንድም የጆሮ ሀኪም የለም። 6ኛ)ስለ አንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ ላይ እንዳልኩት በቆንጆ መልክና በስነ-ስርዓት የተሰሩ ከተማዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበን ጠቁሜያለሁ። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ የከተማና የመንደሮች ሁኔታ ለተመለከተ ግን የማዕከለኛው ዘመን ህዝብ ከሚኖርበት ሁኔታ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የተበላሸ ስዕል ነው የምናየው። ከዚህ ስንነሳ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ሳይሆን ስለ መቆርቆዝና ስለ ኋሊት ጉዞ ነው ማውራት ያለብን።

## ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወይስ ህብረተሰብአዊ ዕድገት!

ከላይ በመጠኑም ቢሆን ለማብራራት እንደሞከርኩት አብዛኛውን ጊዜ ኢኮኖሚ ዕድገት ከጥበባዊ ባህርይው ተለይቶ ስለሚሰላ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ

ትልቅ መወናበድ ይታያል። ጥቂት ከዓለም አቀፋዊ የፊናንስ ኦሊጋርኪ ጋር በጥቅም የተሳሳሩ የሶስተኛው ዓለም አገር ኤሊት ነን ባዮችና የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች በሚያደርጉት ማወናበድ ፣ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ የሰው ልጅ ወደ ባርነት ከተለወጠ ዘመናት አልፏል። በቀላሉ ሊሰራቸውና ኑሮውን ሊያሻሽል የሚችልባቸው ነገሮች ሁሉ ተዘግተውበታል። የአንድ አገር ሀብት በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ስር በመዋል እንዲባክንና በቢሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ማግኘት ያለበትን ነገሮች እንዳያገኝ ተደርጓል። በተለይም ባለፈው አስራ አምስት ዐመት በመዋዕለ-ነዋይና በግሎባላይዜሽን ስም ዓለም አቀፋዊ ዘረፋ እየተካሄደ ነው። በጥሬ ሀብት ዘረፋነት የተነሳ ብዙ የአፍሪቃ አገሮች ወደ በረሀነትና ወደ መበላሸት እያመሩ ነው። በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የጽዳት ዘመቻ እስካልተካሄደ ድረስ ብዙ የጥሬ ሀብት ቦታዎች ወደ መርዛማነት እየተለወጡ ነው። ይህ ሁኔታ አገራችንንም ወደ ፊት የሚመለከት ጉዳይ ነው። ደንታ የሌለው የዛሬው ዐይነት የአገራችን አገዛዝና ጭንቅላታቸው የተሰለቡ ኤሊት ነን ባዮች አገሪቱን ለውጭ "ኢንቬስተሮች" እየለኩ በመስጠት ህዝቦቿን መኖሪያ እያሳጡ ነው። ዶላርና ኦይሮ ሲያዩ ዐይናቸው የሚቀላ መሪዎችና ኤሊቶች ፣ ከህፃናት እስከ ሽማግሌ ፣ ከሴት እስከውንድ ድረስ ወደፊት ፍዳቸውን እያዩ የሚኖሩባትን አገር እያዘጋጁላቸው እንደሆን ካሁኑ በቅጡ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህ ሁሉ የሚካሄደው በዚህ በፈረደበት የኢኮኖሚ ዕድገት ስም ነው። ይህንን የኒዎ-ሊበራሎችንና መሪዎቻቸውን አገር የማጥፋት ህልም መስበር የጊዜው አንገብጋቢ ጠያቂ ነው።

ይህን ማድረግ የሚቻለው እኛ ራሳችንም ከተሳሳተ የኒዎ-ሊበራል ወይም የነጻ የገበያ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ስንላቀቅና ስለህብረተሰብ ዕድገት ያለን አስተሳሰብ ግልጽ የሆነ እንደሆንና ፣ በሬናሳንስ የኢኮኖሚ ቲዎሪ ላይ የተደገፈ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ያደርግን እንደሆን ብቻ ነው። የሰው ልጅን የመፍጠር ችሎታ ቀዳሚ ቦታ የሰጠንና በዕውነተኛ ፍልስፍና የተመራን እንደሆን ከአንድ ነገር በመቶ የሚቆጠሩ ነገሮች ማምረት እንችላለን። ይሁንና ግን ፣ ዛሬ በዓለም አቀፍ የተስፋፋው የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ምሁሩንና ሰፊውን በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ እያራራቀው መጥቷል። በኒዎ-ሊበራል ወይም በፖዘቲቭ ሳይንስ የሰለጠነው እኔን የመሳሰለው ምሁር ለህዝባችን ትክክለኛውን የስልጣኔ ፈልግ ከማሳየት ይልቅ በራሱ ዓለም ውስጥ እየኖረ በተጨባጭ ለጽረ-ዕድገት አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። ስለዚህም በህብረተሰብና በአኮኖሚ ዕድገት ላይ የጠራ አመለካከት እስከሌለን ድረስ እኛም ከኢህአዴግ የተሻለ ስራ አንሰራም ማለት ነው። እኛም ዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ከሚሰጡን መመሪያ አናልፍም ማለት ነው። ቢያንስ አምስት መቶ ዐመት የተካሄደው የኢኮኖሚ ዕድገትንና ህብረተሰብን የመገንባት ትግል የሚያረጋግጠው ፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ሁል ጊዜ ተጻራሪ ኃይሎች ይኖራሉ። በዛሬው እጅግ በተወናበደው የዓለም ሁኔታ ደግሞ ትግሉ እጅግ አከራካሪና አስመራሪ ይሆናል። እኛን የመሳሰሉ ደካማ አገሮችን ባለንበት ለማስቀረትና ባርያ እንድንሆን ለማድረግ የውጭ ኃይሎች በአሸበረቁና በተወሳሰቡ ፣ ነገር ግን ደግሞ ችግርን በማይፈቱ ሞዴሎች እያታለሉንና ጥቂት የውስጥ አርበኞችን ተገን በማድረግ ወደ ፊት የገፋ ትግል ያደርጋሉ። ህዝብም ዕውነተኛ የስልጣኔ ብርሃን እንዳይፈናጠቅበት ያልተቆጠበ ትግል ያደርጋሉ። ማንነቱን እንዳያውቅና በራሱ ላይ ዕምነት እንዳይኖረው የማይሸርቡት ሴራ የለም። በሳይንስ ስም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠርን እንደኔ ያለውን ኤሊት ነን ባይ በማወናበድ አንድ አገር ታሪክ እንዳይሰራ ያደርጋሉ። እነ ዶክተር ሄለኔና በኮሜዲቲ ገበያው እዳራሽ ውስጥ ኮምፕዩተር ፊት ለፊት ተቀምጠው ቁልጭ ቁልጭ የሚሉትና ሰማያዊ ዩኒፎርም ለብሰው እዚህና እዚያ የሚራወጡት አዲስ ወጣት ነጋዴዎች በዚህ የኢምፕሬሲስት ወይም ፖዘቲቭ ሳይንስ የተወናበዱ አዲስ ነጋዴዎችና የስልጣኔ ጠንቆች ናቸው። የድህነቱን ዘመን የሚያራዝሙና በሺህ ድሮች ከዓለም አቀፋዊ የፊናንስ ኦሊጋርኪ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። በ1980ዎቹ አርጀንቲና በራሷ ሀርቫርድ በተማሩ ኤሊቶች ከፊናንስ ኦሊጋርኪ ጋር በማበር እንዳፈራረሷትና እስከዛሬም ከመርዙ ለመላቀቅ እንዳልቻለች ሁሉ ፣ እኛም እንደዚህ ባሉ በተሸብረቀረቁ ዘመናዊያን ፍዳችንን እናያለን ማለት ነው።

ስለሆነም ኢኮኖሚ ዕድገት ምን ማለት ነው? አንድ ህብረተሰብስ ጤናማ በሆነ መልክ እንዴት ነው የሚገነባው? በህብረተሰብና በኢኮኖሚ ዕድገት መሀከል የሚኖረው ውስጣዊ ግኑኝነት ምንድን ነው? እያልን እየመላለስን መጠየቅና ለችግራችንም መፍትሄ መስጠት አለብን። በመሆኑም ግለሰቦች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና ፣ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ዕድገት(Knowledge Based Economic Development) ምን ማለት ነው? ምንስ ይመስላል? ብለን በመጠየቅ ዓለም አቀፋዊ የፊናንስ ኦሊጋርኪ ከደገሰልን ድግስ ለመላቀቅ መዘጋጀት አለብን። እየመላለስን ጥያቄ በመጠየቅና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተንሰራፋውን ድህነትና እንዲሁም መተረማመስ ስንመረምርና ራሳችንንም ስንጠይቅ በእርግጥም የሰብአዊነት ባህርይ እንዳለን መረዳት

እንችላለን። ስለዚህም ስለኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ በመጀመሪያ ደረጃ ከቀላልና ከመሰረታዊ ነገሮች መነሳት አለብን። 1ኛ)የሰው ልጅ ማሰብና መስራት እንዲችል በመጀመሪያ በበቂው መመገብ አለበት።ለመኪና ማንቀሳቀሺያ ከሌሎች ነገሮች ባሻገር ነዳጅ እንደሚያስፈልገውና ሌሎች ማሽኖችም ካለ ኃይል መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ሁሉ ፣ የሰው ልጅም ኃይል ሊያገኝ የሚችለው በበቂው ብቻ ሳይሆን ፣ ጥራት ያለውም ምግብ የተመገበ እንደሆን ብቻ ነው። በማሰብና ጥሩ ምግብ በመመገብ መሀከል ግኑኝነት እንዳለ የታወቀ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ንጹህ ውሀ ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው። 2ኛ)ለሰው ልጅ ከምግብ ባሻገርም መጠለያ ያስፈልገዋል። መጠለያ ሲባል ጎጆ ቤት አይደለም ወይም ሳር ቤት አይደለም። ለማንኛውም ዜጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የሚሰራ መጠለያ ወይም ቤት ያስፈልገዋል። በአንድ ጎጆ ውስጥ አስር ሰው ተጨናንቆ የሚኖር ከሆነ ይህ ዓይነቱ ኑሮ ከሲኦል አይሻልም። የሰው ልጅ የበለጠ ማሰብና ሊፈጥር የሚችለው የቤት አሰራሩንም የለወጠ እንደሆንና ተደላድሎ መኖር የቻለ እንደሆን ብቻ ነው። ይህንን ስንመለከት ፣ በብዙ የኢትዮጵያ ገጠሮች አዲስ አበባንም ጨምሮ ብዙ ሰው በአንድ ክፍል እየተጨናነቀ እንዲኖር ተደርጓል። በተለይም በዚህ ዐይነት ሁኔታ ህፃናት ጤናማ ዕድገት ሊኖራቸው አይችልም። 3ኛ) ለአንድ ህብረተሰብ ከሁኔታው ጋር ሊጓዝ የሚችል የኃይል ማመንጫ በየጊዜው መፍጠርና ማስፋፋት ያስፈልጋል። ካለ ኃይል መቀቀል አይቻልም። ካለ ኃይል ማታ መብራት ማግኘትና በተለይም ወጣቱ ሊያጠና አይችልም። በተጨማሪም መብራት የሰውን ልጅ ከአደጋ የሚከላከል ነው። በአገዛዙ የተሳሳተ የዕድገት ፖሊሲ የተነሳ አሁንም የአገራችን ህዝብ ይህንን መሰረታዊ ፍላጎት እንዳያገኝ ተደርጓል። ቴክኖሎጂ በተስፋፋበት በዛሬው ዓለም ኃይልን ከጸሀይና ከነፋስ እንዲሁም እንደገና በጥቅም ላይ ከሚውሉ የጥሬ ሀብቶች ማምረት ይቻላል። በኃይል ችግር የተነሳ በዛፍ ቆረጣ አገሪቱ ወደ ምድረበዳነት እየተለወጠች ነው። 4ኛ)ለአንድ ህብረተሰብ ላይ ከተጠቀሱት ነገሮች ባሻገር የህክምና ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተለይም በዛሬው አዳዲስ በሽታዎች እየተከሰቱ በሚመጡበት ዓለምና የህዝብ ቁጥር በሚጨምርበት ዘመን ከጊዜው ጋር የሚሄድ የክሊኒክና የጤና ጣቢዎች ማዘጋጀት ያስፈልጋል። አምራችና ማሰብ የሚችል ህዝብ እንዲኖረን ከፈለግን ከዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ልናልፍ እንችልም። ይሁንና ገን ዛሬ አገራችን እንደምናየው ፣ እንደምንም በዚህ ላይ ከመረባረብና ፣ በዚህም በዚያም ብሎ የህክምና መሳሪያዎች ራሳችን ለማምረት ከመሯሯጥ ይልቅ መንግስት የምጣኔ ሀብትን እያባከነና ህዝቡን ለበሽታ እያዳረገው ነው። የአገር ባህል መድሀኒቶች ሳይንሳዊ በሆነ መልክ እንዳይጠኑና ለህዝቡ እንዳይቀርቡ በሆነው ባልሆነው መንገድ እየተዘጋ ነው። በዚህ ረገድ ብዙ ነገር ሊሰራና ህዝቡንም ከበሽታ ማስታገስ ሲቻል ፣ የጤና ጥበቃ ሚንስተር ኃላፊነቱን ሊወጣ አልቻለም። እነዚህ መሰረታዊ ነገሮችና ንጹህ ውሀ በሌለበት አገር ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት በፍጹም አይቻልም። እነዚህን ነገሮች ከማሟላትና ኢንቬስተሮችንም በተለይም የህክምና ማምረቻ መሳሪያዎች እንዲያቋቁሙ ከመገፋፋት ይልቅ የኮካኮላና የቢራ ፋብሪካ እየተስፋፋ ሀብት እንዲባክንና ዕውቀት እንዳይስፋፋ መንገዱ ሁሉ እንዲዘጋ እየተደረገ ነው። ስለዚህም ፣ የወደፊቱ አገዛዝ ቅድሚያ እነዚህን መሰረታዊ ፍላጎቲች ለማሟላትና ሌሎች ሰፋ ያለ መሰረት ሊጥሉ የሚችሉ የኢኮኖሚ ክንውኖች ላይ መሰማራት ይሆናል ማለት ነው። የዛሬው አገዛዝ ታሪካዊ ሚና ተገባዷል። በአስራ ዘጠኝ ዐመት የአገዛዝ ዘመኑ የእነ ዓለም ባንክንና የዓለም የገንዘብ ድርጅትን ትዕዛዝ ከመቀበልና ተግባራዊ ከማድረግ በስተቀር ታሪክን ሊሰራ የማይችል ኃይል መሆኑን አረጋግጧል። ስለዚህ ፣ ከዚህ አገዛዝ ምንም የምንጠብቀው ነገር የለም ማለት ነው። <u>*የወደፊቱም ትግል ታሪክን በመስራትና ባለመስራት ፣ ኢትዮጵያን ታላቅ አገር በማድረግና ባለማድረግ መሀከል የሚካሄድ ትግል ነው። ትግላችን ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜ የኒዎ-ሊበራሊዝምን አስተሳሰብ ደምስሰን በሬናሳንሰ ኢኮኖሚ ፍልስፍና እየተመራን አገር የምንገነባበት ዘመን ይሆናል። ትግላችን ከዚህ በታች ሊሆን አይችልም። መልካም ንባብ!*</u>

1. የዱርዬ ከበርቴ የሚለው አነጋገር በታወቁት የአማሪካን ኢኮኖሚስትና የላቲን አሜሪካ ኤክስፐርት የነበሩት በፕሮፌሰር አንድሬ ጉንደር ፍራንክ ለብዙ የላቲን አሜሪካ አገር አጥፊዎችና የአሜሪካ ተላላኪዎች ባለሀብቶች የተሰጠ መጠሪያ ስም ነው።

2. ፕሮፌሰር ኤሪክ ራይነርት እጅግ ግሩም በሆኑ ጽሁፎቻቸውና መጽሀፋቸው እንዳረጋገጡት ፣ የኒዎ-ሊበራሊዝምና የኋልኛው አዳም ስሚዝ ቲዎሪ በአሸናፊነት ከወጡበት ጊዜ ከ1880 ዓ.ጀምሮ ዕውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገትና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቲዎሪ በየዩኒቨርሲቲዎቹ አይሰጡም። በዚህም ምክንያት በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚካሄዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተብለው የሚጠሩ ሳይሆን አገርን

**የሚያጠፉ ናቸው። በ** Professor Erik Reinert **የተጻፉትን አያሌ ጽሁፎችና** How Rich Countries got Rich and why Poor countries stay Poor! **የሚለውን አዲሱን መጽሀፋቸውን ለተመለከተ በጣም ጥሩ ትምህርት ሊያገኝበት ይችላል። በተጨማሪም የፍሪድሪሽ ሊስት ፣የሹምፔተር ፣የሮሸና ሶምባርትና ላይብኒዝ የኢኮኖሚ ጽሁፎች ለዕውነተኛ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መመሪያዎች ናቸው።**

**ፈቃዱ በቀለ**
fekadubekele@gmx.de